# <u>ቀጣዩን ትውልድ ለመታደግ ቁጠባን ለውሃ</u>

*በመዓዛ ከበደ፣ ከኮዋሽ ፕሮጀክት*

**ትዝታ እንደ መግቢያ** - ከእለታት በአንዱ ቀን ከትምህርት ቤት ጓደኛዬ ጋር ወደ ምግብ አዳራሽ በሚወስደው መንገድ ላይ በአጠገባችን የሚያልፉ ተማሪዎች አጥርተው ሊሰሙት በሚችሉት ድምጽ የምሬትም የሐሜትም የሚመስሉ ቃላትን በማከታተል እናወራለን፤ እንዲህ ስንል

*... ትቅራ፡ የቀረች እንደሆነስ፤ መሞት አለብን እንዴ! ይኸው እስከ አሁን ድረስ ጠበቅናት፤ አልመጣችም፤ ምነው አሁንስ አልበዛም! መቼም ያለ እኔ አይሆንላቸውም ብላ ነው እንዲህ የምትቀልድብን፤ ትቅር፣ ኧረ ትቅር፤ ከእንግዲህ እሷን በመጠበቅ ....*

አልፎ ሂያጁ የምንናገረውን በጨረፍታ ሰምቶ የትኛዋ ጓደኛቸው ላይ ይሆን ይሄን ያህል የሚዝቱት በሚል መልክ ገሚሱ እየገላመጠን ገሚሱም በትዝብት እራሱን እየነቀነቀ ሲያልፈን ለእኔና ለጓደኛዬ ጥሩ የንዴት ማብረጃ ትእይንት ነበር፡፡ እኛ እኮ እምናወራው ስለ ሌላ ጓደኛችን ሳይሆን ወትሮ በቧንቧ የምትመጣው ውሃ በመቅረቷ ርእሰ ፉከራችን ውሃይቱ ነበረች፡፡

**ሐተታ** - በአየርላንድ ዋና ከተማ ዱብሊን እ.ኤ.አ በጃንዋሪ 31፣ 1992 ዓ.ም የተካሄደው የውሃ ባለሙያዎች ስብሰባ "ውሃና ዘላቂ ልማትን በተመለከተ የዱብሊን መግለጫ" በመባል የሚታወቀውን የሥራ መርህ ግብር ይፋ ማድረጉ ይታወሳል፡፡ ይኸው ስብሰባ በአጭር ቃል " የዱብሊን መርህ" መባሉንም ልብ ይሏል፡፡ ስብሰባው ውሃን ለተለያየ አገልግሎት ለመጠቀም ያለውን ያልተገደበ ፍላጎትና ለዚህም ሲባል ይህን የተፈጥሮ ሃብት አሚጦ መጠቀም የሚያስከትለውን የውሃ እጥረት ችግር ከዘላቂ ልማት ጋር በማያያዝ አጉልቶ ያሳየ ነበር፡፡ በወቅቱም የችግሩን ጥልቀትና ስፋት ለመቀነስ በየደረጃው በሚገኙ ባለድርሻ አካላት ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባው መርሃ ግብር የተነደፈ ሲሆን በዋናነት በአራት መሠረታዊ ነጥቦች የሚጠቃለል ይሆናል፡፡ እነዚህም፣

1/ ጨዋማ ያልሆነ ውሃ ህይወትን፣ ልማትንና አካባቢን ለማኖር አስፈላጊ ሲሆን ይህ ሀብት አላቂና ለጉዳት ተጋላጭ መሆኑን መረዳት፤

2/ በውሃ ልማትና አስተዳደር ሥራ የተጠቃሚዎች፣ የእቅድ ዝግጅት ባለሙያዎችና የፖሊሲ አውጪዎች የጋራ ተሳትፎ አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ፤

3/ ሴቶች ውሃን በማቅረብ፣ በማስተዳደርና በመጠበቅ ረገድ ከፍተኛ ሚና ያላቸው መሆኑን እውቅና መስጠትና፣

4/ ውሃ ጥቅም ላይ በሚውልበት አገልግሎት ሁሉ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ያለው በመሆኑ እንደ ምርት / ሸቀጥ ሊወሰድ ይገባል የሚሉት ናቸው፡፡

እርግጥ ነው ውሃን ካለው ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ጋር ብቻ ማያያዝ ሰብዓዊ መብትን በተሟላ መልኩ ለማረጋገጥ እንቅፋት መሆኑን በመረዳት እ.ኤ.አ በኖቬምበር 2002 ዓ.ም በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና የባህል መብቶች ኮሚቴ ማንኛውም ሰው በቂ፣ አስተማማኝ፣ ተቀባይነት ያለው፣ ተደራሽ የሆነና እና በተመጣጣኝ ዋጋ ውሃ የማግኘት መብት እንዳለው አካትቷል፡፡

እንግዲህ - ውሃ ገንዘብ ነው ፤ እንዲሁም ውሃ ለሰብዓዊ መብት መከበር አንኳር ድርሻ ያለው ነው በሚለው አለም አቀፋዊ እሳቤ ከተግባባን ጥቂት ማለት ወደፈቀድኩበት ርእስ ልሻገር፡፡ ውሃ አላቂ ነው ወደሚለው አስደንጋጭ እውነታ!

አገራት ለዜጎቻቸው ፍላጎቶች መሟላት በሚያደርጉት ጥረትና በደረሱበት የእድገት ደረጃ ለኑሮ አመቺ መሆናቸው ታሳቢ ተደርጎ ቅደም ተከተል ሲወጣላቸው እንመለከታለን፡፡ ከነዚህ መሰረታዊ ፍላጎቶች መካከልም የውሃ ሽፋን እንደ አንድ ቀዳሚ መስፈርት መካተት መቻሉ ብዙም አስገራሚ አይሆንም፡፡ ለዚህም ነው በአገራችን በኢትዮጵያም የውሃ ሽፋንን ለማሳደግ በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ በገጠርና በከተማ ሊደረስበት የሚገባውን ግብ በማስቀመጥ ለግቡ ስኬት እየተሰራ ያለው፡፡ እሰየው! ይሄን ማን ከፉ ብሎት!

ታዲያ የውሃ ሽፋንን ከማሳደግ ጎን ለጎን ውሃን በአግባብ ስለ መጠቀም መነጋገር አይኖርብን ይሆን? ይልቁንም በከተሞች አካባቢ "የተጣራ ንጹህ ውሃ" መጠቀም የግድ ለማይሉ ተግባራት ጭምር ያለ ከልካይ ጥቅም ላይ ስናውለው ይታያል፡፡ ለምሳሌም፣ በግንባታ ላይ ያሉ ሕንጻዎችን ለማጠጣት፣ መኪና ለማጠብ፣ የግቢ ንጣፍ፣ ምንጣፍና የመሳሰሉትን ለማጠብ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ ለመጸዳጃ ቤት ቆሻሻ ማስወገጃ የምንጠቀመውም ውሃ የተለየ አይደለም (እዚህ ላይ ፍሳሽን አጠራቅሞ እንደገና ጥቅም ላይ እንዲውል እየተደረገ ያለውን የመንግስት ጥረት ማድነቅ ተገቢ ይሆናል)፡፡ የብክነቱን መጠን ብዙ ባናስተውለውም በቧንቧ እቃዎች ብልሽት ምክንያት እየተንጠባጠበ የሚባክነው የውሃ መጠንም ብዙ ነው፡፡ ለነገሩማ የገንዘብ ቁጠባን አስፈላጊነት ለማስተማር የገንዘብ ተቋማት የሚጠቀሙት ምስል የውሃ ጠብታ መሆኑ መቼ ጠፋን፡፡ ጠብ፣ ጠብ፣ ጠብ፣ እያለ የሚጠራቀም ውሃ በጊዜ ሂደት ባልዲውን

እንደሚሞላ ጥቂት በጥቂት የሚቆጠብ ገንዘብም ሲጠራቀም ቁም ነገር ይሰራል የሚለውን ለማስረዳት እንደማለት ነው፡፡ ወደ ውሃ ብክነት ጉዳያችን እንመለስና፣ በየቤታችን ያለንን የውሃ አጠቃቀም ስናስብ ቀድሞ የሚታወሰን "ለምንጠቀመው ውሃ በቆጠረው መጠን ክፍያ እንፈጽማለን፣ ስለዚህ ተወቃሽ አንሆንም" የሚል ሊሆን ይችላል፡፡ የክፍያው ተመጣጣኝነት የቱንም ያህል ቢሆን በንጹህ ውሃ እጥረት የሚንገላታውን ሌላውን የህብረተሰብ ክፍል ስንመለከት፣ ለተወሰነ ሰዓት ወይም ቀናትም ቢሆን የውሃ መቋረጥ ሲያጋጥመን የሚኖረንን ጭንቀት ስናስብ፣ ከሁሉም በላይ አላቂ ነው የተባለውን ሀብት ያለአግባብ ጥቅም ላይ ማዋላችንን ስንረዳ "አማራጭ ይኖር ይሆን? ብለን መጠየቃችን አይቀርም፡፡ መቼም... በእለት ተእለት ኑሮአችን የሚያጋጥሙንን ኩነቶች፤ በግድ የተመራማሪዎች የጥናት ውጤት ተደርጎ፣ በትልልቅ ድርሳን ተደጉሶ፣ በአለም አቀፍ መድረክ የመወያያ ርእስ ሆኖ ይቅረብልን አንልም፡፡ ምክንያቱም ማየት ማመን ነውና፡፡ ስለሆነም ውሃ አላቂ መሆኑን ለማወቅ በዱብሊን ስብሰባ ላይ መገኘት የግድ አይለንም፡፡ በርካታ የአገራችን የውሃ መገኛዎች በአንድ ወቅት ውሃ መያዛቸውን እስከምንጠራጠር ድረስ ደርቀው አጋጥሞናልና፡፡ እናስ? ሳይቃጠል በቅጠል! በችግሩ መኖር መተማመን በራሱ የመፍትሔው 50% ነው ይባል የለም፡፡ ከተማመንን ማለቴ ነው፡፡

***መደምደሚያ*** - ውሃን በቁጠባ መጠቀም ከየራሳችን ይጀምራል፡፡ በቤታችን፣ በመንደራችን፣ በቢሮአችን አለአግባብ የምናፋስሰውን ውሃ በቁጠባ በመጠቀም ለአሁኑ ብቻ ሳይሆን ለመጪው ትውልድም አሳቢ መሆናችንን ማሳየት ይኖርብናል፡፡ በተለይም በብዙ ወጪና ልፋት በየደጃፋችን የሚመጣውን ንጹህ ውሃ በተገቢው መንገድ ለመጠቀም አማራጭ የውሃ አጠቃቀም ስርዓት አዋጭ በሆነ መንገድ ለመጠቀም የሚያስችል አሰራር ቢዘረጋ መልካም ይሆናል፡፡ ለምሳሌ፣ በመዲናችን አዲስ አበባ በርካታ ቁጥር ያለው ተሽከርካሪ እንደመኖሩ በየአካባቢው ለዚህ ጥቅም የሚውል የውሃ አማራጭ ቢኖር ከመፍትሔዎቹ አንዱ ሊሆን ይችላል፡፡ ዛሬ ላይ ከፍተኛ የውሃ ተጠቃሚ የሆኑ ተቋማት የየራሳቸውን ጉድጓድ እንዲቆፍሩ በመንግስት በኩል ጥሪ እንደቀረበ ሁሉ ይህንኑ ጥሪ ወደ ታች በማውረድ ምላሽ ለመስጠት ቢሞከርስ የማይቻል ይሆን ይሆን? እስከዚያው፣ በቤታችንና በቢሮአችን ያሉትን ጥገና የሚሹ የውሃ መስመሮች / ቧንቧዎች በመጠገን ዓይናችን የሚያየውን የውሃ ብክነት ብናስቀርስ፡፡ እኔ ይህንን አልኩ፣ እናንተስ?